## <u>መንግሥት እንዳላየ ዝምታን ለመረጠበት ረሀብ የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ የእርዳታ እጁን ይዘርጋ!</u>

## <u>በወቅታዊ ጉዳይ ላይ</u>

## <u>ከመኢአድ፣ ኢሕአፓ፣ የዐማራ ግዮናዊ ንቅናቄ፣ አንድ ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲና እናት ፓርቲ የተሰጠ መግለጫ</u>

የዛሬዎቹ ገዥዎች ካለፉት ሊማሩ በተገባ ነበር። የኢትዮጵያ ሕዝብ ርኅራሄ በማያውቁ፣ ለሕዝብ ችግር፣ ረሃብ፣ በጠኔ ማለቅ ፍጹም ደንታ በሌላቸው ገዥዎች እጅ ለመከራ፣ ለረሃብና ችጋር ተዳርጎ ይገኛል። ባለፉት ጥቂት ዓመታት በተለይ በሶማሌ ክልልና በኦሮሚያ ክልል የተከሰተው ድርቅ ባስከተለው ረሃብና ችግር በርካታ ወገኖቻችን አልቀዋል የአርብቶ አደሩ ህዝባችን ከብቶች ረግፈዋል። ድርቁ የአገራችንን "የብልጽግና ጎዳና ስለሚያጠለሽ" ስላደረሰው ጉዳት የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲሰማው አልተፈለገም ወይንም የሕዝብ ቁጥር መቀነሻ አንደኛው መንገድ ሆኖ ተቆጥሯል። ዛሬ ደግሞ በሰሜኑ የአገራችን ክፍል በነበረው ጦርነት የአምራቹ ሃይል በጦርነት መማገድ፣የርሻና የምርት ወቅቶችን ለዓመታት በውጊያ ማባከን፣የሠላም መጥፋት፣ በጦር አበጋዞች መመሪያ መሠረት የእርሻ በሬዎች ታርዶ መበላትና መረሸን፣ የእህል ማሳዎች መጋየት፣ ... ትግራይን፣ የአማራ ክልልን፣ አፋርን፣ ... ድቅቅ አድርጓቸው፣ ህዝቡን አደህይቶ ተረጅ አድርጓል። ድርቅ ባይኖር እንኳን ሠላም በሌለበት እንዴት ማምረት ይቻላል? የትግራይና የአማራ ሕዝብ በተከታታይ በተካሄደውና እበአማራ ክልል አሁንም እየተካሄደ ባለው ጦርነትና በተለያዩ ቦታዎች በተከሰተው ድርቅ ምክንያት ለከፍተኛ ረሃብ ተዳርጓል ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸው ወገኖቻችን በረሃብ ምክንያት ሞተዋል እየሞቱም ይገኛሉ።

ያለፉት ሃምሳ ዓመታት ታሪካችንን መለስ ብለን ስንመለከት ንጉሠ ነገሥቱን በግራ ዘመም ፓለቲካዊ እንቅስቃሴ ከስልጣን ለማውርድ በ፲፱፻፷፮ ዓ.ም. በወሎ ጠቅላይ ግዛት የተከሰተውን ድርቅ እና ይኸው ያስከተለውን ረሃብ አንድ ምክንያት

አድርጎ የተጠቀመበት ወታደራዊ መንግስት ብዙም ሳይቆይ በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. የሚሊዮኖችን ሕይወት የቀጠፈውን በድርቅ ምክንያት የተፈጠረ ረሀብ ወደ ጎን ትቶ የፓርቲ ምስረታ ድግስ በመደገስና ፌሽታ በማድረግ ለከፍተኛ ወቀሳ፣ ብሎም ለማይቀረው ውድቀቱ በቅቷል።

ተከታታይ የአገራችን ገዥዎች "ከበሮ ሲያዩት ያምር፤ ሲይዙት ያደናግር" እንዲሉ ካለፉት እና ከተኳቸው ገዥዎች የማይማሩ፤ ያለፉት እና የተኳቸውን ገዥዎች ስህተት እና ወንጀል ደግመው የሚተገብሩ በመሆናቸው ሕዝብ እንዲነሳባቸው ብሎም ሥልጣናቸውን በኃይል እንዲቀማቸው እራሳቸው ምክንያት ፈጣሪዎች ሆነው እስከአለንበት ወቅት ደርሰናል። ዛሬ ጦርነቱም፣ ድርቅም፣ ተባይም፣ መፈናቀልም ባጠቃቸው በትግራይና በአማራ ክልሎች የተከሰተው ድርቅ እና ያስከተለው ረሃብ የብዙ ዜጎቻችንን ሕይወት እየቀጠፈ ይገኛል። ይህ ረሃብ የተከሰተው በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያ ስንዴ አምርታ ዉደ ውጭ አገር ላከች በተባለበት ዓመት ሲሆን የብልጽግናው መንግሥት "በብልጽግና ጎዳና የሚመራትን አገር ገጽታ ላለማጠልሸት" ከሕዝባችን በረሃብ መርገፍ ፊቱን ዞር አድርጓል ምንም እንዳልተፈጠረ ለማስመሰልም እየሠራ ይገኛል። የድርቅ አደጋ ያልደረሰበት ሕዝባችንም ቢሆን ከአቅም በላይ ከሆነ የኑሮ ውድነት ጋር ተጋፍጦ በብዙ ሚልየኖች የሚቆጠረው ለስውር ረሃብ ተዳርጓል።

የድርቅ አደጋ ባጋጠማቸው አካባቢዎች የተከሰተው ችግር መንግሥት ከወራት በፊት በአማራ ክልል በከፈተው ጦርነትና ይህንኑ ተከትሎ በተከሰተው የእንቅስቃሴ መገደብ ይበልጥ ተወሳስቧል። የተከሰተው ረሃብ የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ አስቸኳይ ትኩረት ተችሮት መፍትሄ ካላገኘ ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸው ወገኖቻችንን ሕይወት መቅጠፉ አይቀሬ ነው።

ስለዚህም

- በአንድ በኩል የጠመንጃ አረር በሌላ በኩል ከድርቅ አደጋ ጋር እንዲጋፈጥ ለተደረገው ሕዝባችን የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ የእርዳታ እጁን በአስቸኳይ እንዲዘረጋ ተማጽኖአችንን እናቀርባለን፤
- የእርዳታ ሰጪ ሠራተኞች በየቦታው ተንቀሳቅሰው የሞት አደጋ ላንዣበበበት

ሕዝባችን የነፍስ አድን እርዳታ እንዲያደርሱ ከአደጋ ስጋት ነጻ በሆነ መልኩ እንዲንቀሳቀሱ ሁሉም አካላት አስፈላጊውን እንዲያደርጉ እንጠይቃለን፤

- የኢትዮጵያ ሕዝብ እያለፍክ ያለህበትን የሰቆቃ ኑሮ የምንረዳው ቢሆንም ከትርፍህ ሳይሆን ከጉድለትህ ቆርሰህ በረሃብ ምክንያት የሞት አደጋ ያንዣበበባቸው ወገኖችህን ህይወት በመታደግ እጅ ለእጅ ተያይዘህ ይህን ክፉ ቀን እንድትሻገር የተማጽኖ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ይጠብቅ

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ጥቅምት ፱ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም.

መኢአድ፣ ኢህአፓ፣ የዐማራ ግዮናዊ ንቅናቄ፣ አንድ ኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ፣ እናት ፓርቲ